# ብርቱካን በሁለት የይቅርታ ስያሜዎች መካከል

አንድ ማህበረሰብ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሽግግር ሲያደርግ ባለፈው ታሪኩ ለዘመናት ያዳበራቸውን ባህሉን ወጉን እና ልማዱን መፈተሽ መተቸት እና መሄስ እጅግ ጠቃሚ ነው ምክንያቱም በበነባሩ ባሄል ወግ እና ልማድ ውስጥ ለዴሞክራሲ ማበብ አዎንታዊ እና አሉታዊ አስተዋፅኦ ያላቸው ባህላዊ እና ልማዳዊ እሴቶች ያሉ በመሆናቸው ነው።

በርካታ የአውሮፓ አገሮች ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ያደረጉት ሽግግር ስኬታማ የሆነው ሽግግር ከማክረጋቸው በፊት በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያካበቱትን ባህላዊ እና ልማዳዊ እሴቶች እየፈተሹ እና እየተቹ ለዴሞክራሲ ስርአት ማበብ መሰረት የሆኑ መደላድሎችን (ቅድመ ሁኔታዎችን) መፍጠር በመቻላቸው እንደ ሆነ ታሪክ ያስረናናል። ይህን እውነታ በተመለከተ ማርቲን ሃይዲገር የተባለው የሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀርመናዊ ፈላስፋ በአንድ ወቅት እንዲህ ብሎ ነበር፡- «ትትኩሮታችንን ሳንሰጠው ያለፍነው ነገር ከፊታችን እንደ ደንቃራ ቆሞ ይጠብቀናል።» ሃይዲገር ይህን ማለቱ ያሳለፍነው የታሪክ ሂደት ደብዛው ጠፍቶ እንደማይቀርና በተወሰነም መልኩ በወደፊት አካሄዳችን ላይ የበኩሉን ድርሻ እንደሚይዝ ለማሰብ ነው።

ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዐት ለመግባት ሙከራ በምናደርግበት ወቅት እንደ አውሮፓውየጣኑ ከቀድሞው ዴሞክራሲያዊ ስርአት በፊት በነበረው እና ዘመነ አብርሆት ወይም «ብርሃነ ህሊና» (Enlightment) በሚሉት የአስተሳሰብ አድማስ ስር አላለፍንም የ18ኛው መቶ ክ/ዘመን ፈላስፋ ኤማኑኤል ካንት ብርሃነ ህሊና የሰው ልጅ ከባህል እና ከልማድ ቀንበር ተላቆ በራሱ የግንዛቤ ጎዳና ውስጥ የገባበት ሲሆን ይኸን ይኸውም ከአእምሯዊ ጨቅላነት ወደ አእምሯዊ ጉልምስና ለመሸጋገር የተጓዘበት ዘመን ነው ይለዋል። ስለሆነም አውሮፓውያኑ ለአንድ ምእተ ዓመት ያህል ያደረጉት የባህል የወግ እና የአመለካከት ፍተሻ ዴሞክራሲያቸውን ቀና ሲያደርገው እኛ ደግሞ እንደ እነርሱ ባህል እና ወጋችን ላይ ተገቢውን ሂስ እና ምርምር ስላላካሄድን የዴሞክራሲ ሂደታችን ላይ እንቅፋት አጋጥሞናል።

ይሁንና ወደ አገራችን የመጀመሪያው የህትመት መሳሪያ ከገባ በኋላ «አእምሮ» እና «ብርሃን እና ሰላም»ን የመሳሰሉ ጋዜጦች ላይ አልፎ አልፎ የዘመናዊነትን ብሂል የሚያስተዋውቁ የባህል ትችቶችን ያቀፉ ጽሁፎች ብቅ ማለታቸው ባይቀርም የህትመቶቹ ቀጣይነት በአጭር ስለ ተቀጨ ተገቢውን ውጤት አላመጣም። ከባህላዊ አመለካከት አካያ እስከ ዛሬ ያልተቸነው እና ለብዙ ዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየው (የኖረው) የሴማውያን እይታ ተብሎ የሚታወቀውን የማኒኪያን አስተሳሰብ ነው። ማኒኬይዝም ዓለም ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ በሁለት ተፃራሪ እና ተፋላሚ ሃይሎች መካከል ተወጥራ ትገኛለች ብሎ ስለሚያምን ሁሉንም ነገር የሚመለከተው በሁለት አጽናፎች ላይ ብቻ ተወስኖ ነው። አ3ነዚህም ብርሃንና ጨለማ በጎ እና ክፉ አጥፊ እና ጠፊ ሰሆኑ እነዚህ ሁለት አጽናፎች የሚጋጩበት እና በአጠቃላ ተቃርኖ የሰፈነባት ዓለም ውስጥ እንዳለን ያቀርባል በሁለቱ አጽናፎች መካከል ያለ ሌላ ሶስተኛ እውነታ ሊኖር አይችልም ብሎ ያምናል። ይህ አይነቱ አመለካከት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚነሱ ባህላዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጥየጣቄዎችን ምላሽ ለመስጠት ከሁለት አጽናፎች ውጭ ለመመልከት አይችልም። ስለሆነም ይህ አይነቱ ግንዛቤ በባህል በስነ ምግባር እና በፖለቲ ህይወት ዙሪያ (ላይ) ተጽእኖውን ያሳርፋል።

የፖለቲካ ገጽታውን እንደ ምሳሌ ሠንወስድ ማኒኬይዝም ፍጹማዊ የፖለቲካ እሴት (Value) አንድ ወጥ የፖለቲካ ትንታኔ አንድ አይነት የታሪክ እይታ ብቻ የሚያስተናግድ አስተሳሰብ ነው። በዚህ አስተሳሰብ መሰረት በፓርቲዎች መካከል የሚነሳ ውድድር ውጤቱ ምንጊዜም ፍጹማዊና ብቸኛ ድል መሆን አለበት። ይህ የማኒኬይዝም አመለካከት በአገራችን ለረጅም ጊዜ_ር ሰዶ የቆየ ባህላዊ መሰረት ያለው ከመሆኑ አኩዋያ

አገራችንን በሚያስተዳድረው ፓርቲ ላይ ብቻ ሳይሆን በተቃዋሚ ፓርቲዎችም ላይ የሚያይ መሰረታዊ ችግር ነው።

ለምሳሌ፡- በ1997 ዓ.ም ምርጫ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ህዝቡ በድምፁ ያጎናፀፋቸውን የፓርላም መቀመጫ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተረክቡ ዲባሉ አሻፈረኝ ማለታቸው የ ፍጹማዊ ድል ሰለባ እንደሆኑ የሚያመለክት ነው። በአንጻሩ በዚሁ ምርጫ ማግስት በመንግስት እና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በተነሳው ውዝግብ ለተፈጸነው ጥፋት የተቃዋሚ ፓርቲውን በህግ ተጠያቂ በማድረግ ፍጹማዊ የፖለቲን ድል አስከብረናል የሚለው የመንግስት እይታም የዚሁ የፍጹማዊ ድል እሴት ሰለባ ተጋሪ መሆኑን ያሳያል።

የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የወ/ት ብርቱንን ሚደቅሳን በድጋሚ የመታሰር ጉዳይ ከላይ በተጠቀሰው መልክ በባህላዊ እና ፖለቲካዊ የአመለካከት ክበብ ውስጥ አስቀምጠን ባናየው የተሸለ ግንዛቤ ላይ እንደርሳለን ብሎ ያምናል። ስለሆነም የወ/ት ብርቱካንን ለእስራት የመዳረግ ጉዳይ በተመለከተ የሚከተሉት ሶስት ነጥቦች ዙሪያ ሃሳቤን አቀርባለሁ።

1ኛ) ወ/ት ብርቱካን «ቃሌ» በሚለው ጽሁፏ ከዚህ ቀደም ታስራ ስለ ተፈታችበት ሂደት የህግ አንድምታ አቅርባለች መንግስትም የራሱን ትንታኔ ማቅረብ ይችል ነበር። ሆኖም ግን ከውይይት ይልቅ መሰርን ስለ መረጠ በአንድ በኩል ወ/ት ብርቱካን ባቀረበችው ትንታኔ ላይ መመርኮዝ በዜጎች መካከል እና ዜጎች ከመንግስት ጋራ ሊኖራቸው የሚችለውን ውይይት እና ክርክር ልናገኝ ባለመቻላችን የዲሞክራሲን ልምድ እንዳናካብት ሆነናል።

2ኛ) የወ/ት ብርቱካንንየእስራት ጉዳይ ከህግ እና ከአጠቃላይ ማህበረሰባዊ ጥቅም (common good) አንጻር መመልከትም ተገቢ ነው። አጠቃላይ ማህበረሰባዊ ጥቅም የሚገልጽ ሲሆን ይህ የጋራ ጥቅም ከአንድ ግለሰብ ቡድን እና የፖለቲካ ፓርቲ . . . ወዘተ ጥቅም በላይ ያለ ነው። ህግ ከሁሉ አስቀድሞ ወደ አጠቃላይ ማህበረሰባዊ ጥቅም የሚመራ እና የሚወስድ ወንገድ (means) ነው። የህግ የሞራል እና የመርህ ትክክለኛነት የሚመዘነውም ለአጠቃላይ ማህበረሰባዊ ጥቅም ከሚሰጠው ፋይዳ አኩዋያ ነው። ወ/ሪት ብርቱካን ስለ ይቅርታው ባቀረበችው አንጻራዊ ትንታኔ ገዥው ፓርቲ «ፍጹማዊ ድል አግኝቼበታለሁ» ያለውን አቀራረብ ጥያቄ ውስጥ አስገብታው እንደ ሆነ ነው እንጂ በምንም መልኩ የማህበረሰቡን አጠቃላይ ጥቅም አልጎዳችም።

3ኛ) ይሄኛው ሀሳብ ለወ/ት ብርቱካን የተደረገው ይቅርታ ከስነ ምግባር እና ከፖለቲካ አኩዋያ ሊያስገኝ የሚገባውን (የሚችለውን) ውጤት የተመለከተ ነው። ይቅርታ በአንድ ማህበረሰብ ታሪክ ውስጥ ያለፉ የታሪክ ጠባሳዎችን ሽሮ እነዚህ የታሪክ ጠባሳዎች በማህበረሰቡ የወደፊት ጉዞ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያሳድር የሚያደርግ ስርዐት ነው። ይቅርታ ከስነ ምግባር አኩዋያ ቂም አምካኝ ሲሆን ከፖለቲካአኩዋያ ደግሞ ወደፊት የማያራምድን መጥፎ ትዝታ (Dictatorship of memory) የሚሽር ነው። ሆኖም መንግስት ወ/ሪት ብርቱካንን ዳግመኛ ሲያስራት በይቅርታ በተሸገርነው ያለፈ ሁኔታ ውስጥ እንድንገባና ወደፊት እንዳንራመድ ሆነናል።

## I ሕግ እንደ ትንታኔ «እንድምታ»

ከሁሉ አስቀድሞ የወ/ት ብርቱካንን ሁኔታ አስመልክቶ ተጨባጭ ጥያቄው ምንድን ነው? እስራትን ምን አመጣው? ብለን ስንነሳ ተቀዳሚ ግንዛቤያችን ጉዳዩ የእውነት ወይም የሀሰት የመካድ እና ያለመካድ ጉዳይ እንዳልሆነ ማየት ይኖርብናል። ዋናው ፍሬ ነገር ይቅርታ ተቀብላ አልተቀበልኩም ማለቷ ላይሆን በመንግስት እና በእርሷ መካከል

የተፈጠረው ውዝግብ ጠብ እና መንስኤ የይቅርታ ሂደቱ ምን ይመስላል ወይም ምን አይነት መልክ ይዞ ተጉዟል በሚለው ላይ ነው።

ከዚህ ስንነሳ ሁለት ተፃራሪ የህግ እንድምታዎችን እናገኛለን። አንደኛው የመንግስት ሲሆን ሌላው የወ/ት ብርቱካን ነው። እንደ መንግስት አቀራረብ «ወ/ት ብርቱካንን ከዚህ ቀደም አስረናታል በወንጀል አስፈርደንባታል ይቅርታ ጠይቃ አላልኩም በምለቷ በድጋሚ ታስራለች።» የሚል ነው። ወ/ት ብርቱካን በበኩሏ «በእርግጥ ታስሬ ቅጣት ተወስኖብኛ ል በሽማግሌዎች አማካይነት ይቅርታ ጠይቄ ከእስር ቤት ተፈትቼያለሁ። የሽምግልናው ሂደት በአዋጅ የተደነገገውን የይቅርታ መስፈርት ተከትሎ የተከናወነ አይደለም። ስለሆነም ህጉ ያስቀመጠውን የይቅርታ ፈለግ ተከትሎ ስላልተከናወነ ከህጉ አንጻር የይቅርታ ትርጓሜው አጠራጣሪ ነው።» የሚል ነው።

መንግስት «ይቅርታ ጠይቃ በይቅርታ የተፈታችመሆኑን ስላልተቀበለች ታስራለች» የሚል አንድ ወጥ ትረካ በብዙሀን መገናኛ ለህዝብ ከማቅረብ ውጭ እርሷ ባቀረበችው ትንታኔ ላይ በመመርኮዝ የራሱን ትንታኔ ለማቅረብ ስላልፈለገ ወ/ሪት ብርቱካን ወዳቀረበችው ትንታኔያዊ አማራጭ እንሸጋገራለን። እንዲሁም የዚህ ጽሁፍ ተቀዳሚ ተግባር ወ/ት ብርቱካን በአዲስ ነገር ላይ «ቃሌ» በሚል ርእስ ያቀረበችው ጽሁፍ የይቅርታውን ሂደት አስመልክቶ ሌላ አማራጭ እይታ እንዲኖረን የሚያደርግ የተለየ የህግ አንድምታ ያለው መሆኑን ማሳየት ነው። ለዚህም አጠር ባለ መልኩ የክርክሯን ሀሳብ እና መንገድ መቃኘቱ ጠቃሚ ነው ብዬ አምናለሁ።

ወደ እርሷ የክርክር ቅኝት ከመግባታችን በፊት «አንድምታ» የሚለው ቃል ከጉዳያችን ጋራ የተያያዘ በመሆኑ ስለ አንድምታ ጠባይ እና ይዘት ጥቂት ልበል። የአገራችን ሊቃውንት እንደሚያስተምሩን አንድምታ ከነጠላ ትርጓሜ ወደ ተለያየ (ፈርጀ ብዙ) ትርጓሜ የምንሸጋገርበት የምስጢር አፈታት እና የመረዳት ዘዴ ነው። ለምሳሌ:- «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይን እና ምድርን ፈጠረ» (ደረቅ ንባብ) የሚለውን ገለጻ ከዚህ አንድ ወጥ ንባብ (ነጠላ ትርጓሜ) ተነስተን እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው አንድም በደግነቱ አንድም በመለኮቱ አንድም በፍላጎቱ . . . ወዘተ እያልን እንድምታውን እናወርዳለን ማለት ነው።

ወደ አውሮፓውያን ባህል ስንዞርም አንድምታ (Hermeneutics) ወሳኝ የሆነ ድርሳናትን የማንበብ የመረዳት እና የመተርጎም ስልት እና ስርአት ነው። በተለይ ከሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ አንድምታ በፍልስፍና አለም ውስጥ ተቀዳሚ የጥናት ርእስ ሆኗል። ሀንዝ-ጊኢርግ ጋደመር የተባለው የሃያኛው መቶ ክ/ዘመን የጀርመን ፈላስፋ አንድምታን አስመልክቶ «Understanding essentially is understanding differently» ይላል። ይህን ማለቱ «አንድን ነገር ተረዳን ስንል ሁኔታው ለሁላችንም አንድ አይነት አረዳድ እና ትርጓሜ ሰጥቶናል ማለት አይደለም» ማለቱ ነው። ይህም አባባል አንድ ወጥ የሆነ ነጠላ እና ለብቻው የቆመ የትርጓሜ እውነታ እንደሌለ ያስተምረናል። ይህም ማለት በእኛም ሆነ በፈረንጆቹ ባህል አንድምታ የትርጓሜ «ባቢሎን» (የትርጓሜ ትርምስምስ) ማለት አለመሆኑንና ቃሉ (Text) የሚለውን ሳንለቅ በስነ አመክንዮ (Reason) የተደገፈ ገለጻ ይዘን መቅረብ ይኖርብናል ማለት ነው።

## ቃሌ

«ቃሌ» በአውሮፓውያንም ሆነ በእኛ ዘንድ ቁልፍ የሆነ ስያሜ ነው። በላቲን (Verum) በግሪክ (Logos) በግእዝ (ቃል) ሲጠቃለል ሶስት ሀሳቦችን የያዘ ነገር ነው። ይኸውም።

*ሀ) መናገር/ማብሰር ለ) መግለጽ ሐ) መተርጎም ሲሆን ሶስቱንም አሰባስቦ በአንድ ላይ ሲቀርብ በአንድ ቃል «አንድምታ» ባላል::*

*ወ/ት ብርቱካን መታሰሯን አስመልክቶ ታህሳስ 18 ቀን 2001 ዓ.ም ታትሞ በወጣው የ አዲስ ነገር ጋዜጣ ቃሌ ብላ ያቀረበችው ጽሁፍ የርእሱ ስም ቃል ሳይሆን ቃሌ መሆኑ እርሷ ላነሳችው ትንታኔ ሌላ ትርጓሜ ሲሰጥ እንደሚችል በመገንዘቧ ነው:: በዚህ ጽሁፏ ወሳኝ የሆኑ ነጥቦችን በማንሳት በአፈታቷ ህጋዊ የይቅርታ ይዘት ላይ ጥያቄ አቅርባለች:: «ይቅርታ» የሚለውን ቃል ህብረተሰቡ በእለት ተእለት ህይወቱ የሚጠቀምበት በህጉ የተሰጠው ስያሜው እና ትርጓሜው ተቀራራቢነት ቢኖረውም ልዩነት እንዳለው ከእርሷ ጽሁፍ ለመረዳት ይቻላል:: ይህንኑ መሰረት አድርገን «ይቅርታ»ን በተመለከተ ከተነሳንበት ጉዳይ አኩዋያ ስናየው አንደኛው በመደበኛው የህግ አቀራረብ ላይ የተመረኮዘ ሲሆን ሁለተኛው ወደ ሽማግሌዎቹ የይቅርታ አቀራረብ መንገድ ይወስደናል::*

*ወ/ት ብርቱካን የይቅርታን መደበኛ የህግ አቀራረብ በተመለከተ የይቅርታ ህጉን መሰረት ያደረገ ይቅርታ አለመካሄዱን ዐዋጅ ቁጥር 595/1996ን ተመርኩዛ አብራርታለች:: በዚህ ማብራሪያዋ በይቅርታ ስነ ስርአት ዐዋጅ ቁጥር 595/1996*

*ሀ) የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ ላይ*
*ለ) ይቅርታው መቼ እና ምንጊዜ መቅረብ እንዳለበት*
*ሐ) ይቅርታው ለማን መቅረብ እንዳለበት በሚከነግጉት አንቀጾች የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ባለሟላ ሁኔተ ይቅርታ የተደረገላት መሆኑን አስረድታለች::*

*«ቃሌ» ላይ እንዳስቀመጠችው በዐዋጁ አንድ ተከሳሽ በህጉ መሰረት የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ ያለበት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳይሆን ለይቅርታ ቦርድ ነው:: በእኛ ጉዳይ ለአገር ሽማግሌዎች የፈረምነውን ሰነድ ለይቅርታ ቦርድ ያቀረቡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ናቸው ይቅርታውንም የጠየቁት እርሳቸው ናቸው ብሎ መከራከርም ይቻል ይሆናል:: ሆኖም ግን በህጉ አግባብ የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ባለጉዳዩ ጠበቃለው ወይም ቤተዘመድ እንጂ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር አይደለም ጥያቄው መቅረብ የሚችለውም በጉዳዩ ፍርድ ቤት ፍርዱን እና ቅጣቱን አጠናቆ ከወሰነ በኋላ እንደ ሆነ በህጉ ተመልክቷል:: በእኛ ጉዳይ ከመነሻው ጉዳዩን በይደቅርታ* (pardon) *የመጨረስ ስምምነት ስላልነበረን ለሽማግሌዎቹ የተፈረመው ሰነድ የተፈረመው ፍርድ ቤት በጉዳዩ የቅጣት ውሳኔ በመስጠቱ በፊት ነው:: ስለዚህ ከዚህ እውነታ በመነሳት በዚህ በህግ በተሰመረ አግባብ የይቅርታ ጥያቄ አላቀረብኩም:: የሚል ነው::*

*ወ/ት ብርቱካን ይህን ማብራሪያ ስትሰጥ በይቅርታ ስና ስርአት ዐዋጁ ላይ የተቀመጡ አንቀጾችን መሰረት አድርጋ ነው:: የጋዜጣውን ዓምድ ላለማጣበብ ታስቦ ነው እንጂ እኒህን አንቀጾችን መጥቀስ ይቻል ነበር::ሆኖም አንቀጾቹን ማየት ለፈለገ በአንቀጽ 02/6 በአንቀጽ 4/6 እና 04/6 ላይ መመልከት ይቻላል::*

*ወ/ት ብርቱካን በጽሁፏ «ይቅርታው በህግ አግባብ አልተካሄደም» ካለች በኋላ በሽማግሌዎቹ በኩል ይቅርታ መካሄደን አልካደችም:: «ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በተጻፈው ሰነድ በሽማግሌዎች አማካይነት መንግስተን እና የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ጠይቄያለሁ::» ብላለች:: እንግዲህ ወ/ት ብርቱካንን ለእስር የዳረጋት መንግስት ካቀረበው ትረካ ሌላ ስለ ነገሩ እኔ የተለየ አንድምታ አለኝ የግል ትንታኔ አለኝ በማለቷ ነው እንጂ ጉዳዩ ይቅርታን ተቀብሎ ስለ መካድ እና ስለ ሽፍጥ አይደለም::*

*ታሪክ እንደሚያስተምረን የሰው ልጅ በፖለቲካ በሃይማኖት በሳይንስ . . . ወዘተ ሁለት ተፃራሪ ሀሳቦች በሚነሱበት ጊዜ ከሁለቱ ሀሳቦች ተቀባይነት የሚያገኘው እውነታን እና*

ሀቅን የማያንፀባርቀው ሃሳብ ሳይሆን ከሁለቱ ተፃራሪ ሀሳቦች በሚነሱበት ጊዜ ከሁለቱ ሀሳቦች ተቀባይነት የሚያገኘው እውነታን እና ሀቅን የማያንጸባርቀው ሀሳብ ሳይሆን ከሁለቱ ተፃራሪ ሀሳቦች ስልጣን እና ጉልበት ባለው ሃይል እንደተመለከትነው የወ/ት ብርቱካንን እና የመንግስትን አቀራረብ አስመልክቶ ከቀረቡት ሁለት የተለያዩ ትንታኔዎች ጉልቶ እንዲሰማ እና ተቀባይነት እንዲኖረው የተደረገው የመንግስት ሀሳብ ነው፡፡

## II ሕግ እና አጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም (Common Good)

ህግ ብዙ ትርጉሞችን ያቀፈ የስርአት እና የደንብ ዘርፍ ነው፡፡ ስለሆነም የህግን ዓለም ለማስረዳትም ሆነ ለመረዳት የተለያ መንገዶች እና አቀራረቦች አሉ፡፡ ከተነሳንበት ርእስ አኳዋያ ህግን የምንመለከተው ለአጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም (Common Good)ከሚያስገኘው ፋይዳ እና ይህን ፋይዳ እውን ለማድረግ ራሱ ህጉ በሚከተለው የአፈጻጸም ስርአት ነው፡፡

## ሀ) አጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም

«አጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም» የሚለው ብሂል (ወግ) የግልን የፓርቲን የሲቪልን ተቋማትን . . . ወዘተ ፍላጎት እና ጥቅም ያካተተ በየጊዜው እንደ ሁኔታው እየታደሰ እና እየተስተካከለ የሚሄድ ፅንስ ሃሳብ ነው፡፡ አጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም የሚለው ፅንሰ ሃሳብ በአንድ ስርአት ውስጥ ያለውን የምርት ግንኙነት የፍትህ ግንኙነት እና የአስተዳደር ግንኙነት አቅፎ የያዘ መርህ ነው፡፡

በተጨማሪ የሕጉ የሞራል ደረጃ እና የመርህ ትክክለኛነት የሚመለጨውም ሆነ የሚመዘነው ከዚሁ አጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም አንጻር ነው፡፡ ህግ አንድ ማህበረሰብ ወደ አጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም ላይ ለመድረስ የሚያስችለውን መንገድ የሚጠቁም የሚያሳይ እና የሚያስገድድ መሳሪያ (means) ነው፡፡

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እያንዳንዱ የማህበረሰብ አባል ቡድን የፖለቲን ፓርቲ . . . ወዘተ በየግላቸው እውን እንዲሆን የሚፈልጉት ጥቅም አላቸው፡፡እያንዳንዱ የማህበረሰብ አባል ቡድን የፖለቲካ ፓርቲ ወዘተ እውን እንዲሆንለት በሚፈልገው ጥቅም እና በአጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም መካከል ግጭት ሲለሳ ህግ የግጭቱ መፍቻ ዋነኛ መሳሪያ ይሆናል፡፡ ህግ መሳሪያነቱ አጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም እውን እንዲሆን ማድረገግ ከመሆኑ አኳዋያ የህግ የበላይነት መከበር ወሳኝነት አለው፡፡

የህግ የበላይነት አልተከበረም ማለት የማህበረሰቡ አባል ቡድን ፖለቲካ ፓርቲ በግሉ እውን እንዲሆንለት  የሚፈልገውን ጥቅም በአጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም ላይ መጫን ማለት ነው፡፡ የወ/ት ብርቱካንን ዳግመኛ እስራት ጉዳይ ስንመለከት ገዥው ፓርቲ የራሱን ጥቅም እንደ አጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም በመውሰድ ፓርቲው ሲነካ አገር የተነካ በማስመሰል የይቅርታ ስነ ስርአት ህጉን በመጣስ የእስራት እርምጃ ወስዶባታል፡፡

## ለ) ሕግ እና ስነ ስርአት

በአንድ በኩል ወ/ሪት ብርቱካን የተፈታሁት የይቅርታ ስነ ስርአት አዋጁን በተከተለ መልኩ አይደለም ስትል ዳግመኛም የዚህኑ አዋጅ ድንጋጌዎች ባልተከተለ መልኩ መታሰሯ የሚያሳዝን ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የአዋጁ ስም የይቅርታ ስነ ስርአት አዋጅ ሆኖ ካለ እርሷን ስነ ስርአት በጎደለው መልኩ ማሰሩ ደግሞ ሌላው እንቆቅልሽ paradox ነው፡፡ በዚህ የህግ ጥያቄ ዙሪያ ከአንድ የህግ አዋቂ ወዳጄ ጋራ ለበርካታ ቀናት ውይይት

ካደረግን በኋላ ተገቢ ናቸው ያላቸውን ነጥቦች በጥያቄ መልክ ጽፎ ስለ ሰጠኝ ጠቃሚነቱን በመገንዘብ አቅርቤያለሁ፡፡

«መንግስት ወ/ት ብርቱካንን ያሰራት የይቅርታ ህጉን ሳይከተል ነው» የሚለው የመከራከሪያ ነጥብ በማሳያነት ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መካከል፡-

(1) 1.በተራ ቁ. 3 የቀረበው ክስ የይቅርታ ቦርዱ የተቀበለው እንደ ሆነ በአዋጁ አንቀጽ 17 (1) እንደተደነገገው «ይቅርታ ለማስረከብ የሚያበቃ ምክንያት» መገኘቱን እና ምክንያቱን ለይቅርታ ባዩ በጥሁፍ ተልኮለታል ወይ?

(2) ደርሶት ከሆነ መልስ የመስጠት መብት ያለው ሲሆን መልሱንም ጽሁፉ በደረሰው ቢበዛ በሃያ ቀን ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ (አንቀጥ17(2))

(3) የይቅርታ ቦርዱ በቅድመ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የተሰጠው ይቅርታ ቅድመ ሁኔታው መጣሉን አረጋግጧል ወይ? (አንቀጽ 16(3))

(4) በተራ ቁጥር 6 እንደተገለጸው የይቅርታ ቦርዱ ቅደመ ሁኔታው ተጥሷል በማለት ለፕሬዝዳንቱ የውሳኔ ሀሳቡን አቅርቧል ወይ?

(5) በይቅርታ ቦርዱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ፕሬዝዳንቱ በአንቀጽ 10(2) ተቀብለውት የተሰጠው ይቅርታ እንዲሰረዝ ወስነዋል ወይ?

የሚሉት ጥያቄዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ መንግስት እነዚህን ከላይ የተነሱትን የህግ ጥያቄዎች በአግባቡ ላለመመለስ እና የይቅርታ ስነ ስርአት ህጉን መጣሱን በቅጡ ለመረዳት ከህግ ክበብ ወጥተን ወዳለንበት የፖለቲካ ሁኔታ መሸጋገር ይኖርብናል፡፡ ማንኛውም መንግስት ልክ እንደ ኤሌክትሪክ ሁለት አይነት ገመድ (current) ላይ የተመሰረተ ሀይል ወስልጣን power ያለው ነው፡፡ ይኸውም አንደኛው ወንዴ ኮረንቲ (positive power) ያለው ገመድ ሲሆን ሁለተኛው ሴቴ ኮረንቲ (negative power) ያለው ገመድ ነው፡፡ እንዲሁም በመንግስት በኩል አንደኛው ገመድ የህግ የአስተዳደር እና የፖለቲን ገመድ ሲሆን ሁለተኛው የሃይል የመቅጫ እና የማረሚያ ገመድ ነው፡፡

ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ባላቸው አገሮች አንደኛው ገመድ ሁለተኛውን ገመድ የማዘዝ እና የመቆጣጠር ስልጣን አለው፡፡ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር በጎደለባቸው አገሮች ግን ሁለተኛው ገመድ የመጦዝ ባህርይ አለው፡፡ በአገራችን ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የመንግስት ሁለተኛው ገመድ በጣም ግሏል፡፡ ለዚህም ነው የወ/ት ብርቱካን እስራት ጉዳይ በአንደኛው ገመድ ሳይሆን በሁለተኛው ገመድ የተፈጸመው፡፡

እዚህ ላይ በ48 ሰዓት ውስጥ የማስተባበያ የጊዜ ገደብ ተሰጥቷት ወደ እስር ቤት መውረዷ የ«ጦቢያ» ልብ ወለድ ደራሲ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ለጣልያን አድረዋል ተብለው የሞት ፍርድ ሲበየንባቸው የተናገሩትን አስታወሰኝ፡፡ ይህን ንግግራቸውን ያነበብኩት የህይወት ውጣ ውረድ በሚለው የከንቲባ ዘውዴ ገ/ህይወት አስገራሚ መጽሀፍ ላይ ሲሆን ፍሬ ሀሳቡን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

> ተሰለጠነና ችሎት ተጠራ ተሰለጠነና ክስ ተነበበ ተሰለጠነና
> መከላከያ አቀርብ ተባልኩ ሆኖም ባንድ እረፋድ የሞት ፍርድ
> በየናችሁብኝ፡፡የምታሳዝኑ ጉድ ናችሁ፡፡

እዚህ ላይ ቁምነገሩ «ባንድ እረፋድ» የሚለው ነጥብ ነው ወ/ሪት ብርቱካንም በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ የእድሜ ልክ እስራት ተበይኖባታል፡፡

## ሐ) ሕግ እና ትንታኔ

ህግ በአንድ በኩል ለሁኔታ ተጠሪ በሌላ በኩል በውስጡ በያዛቸው አንቀጾች ዳኝነት ላይ የተመሰረተ ነው:: ለዚህም ነው በአንድ ወቅት ተገቢ ነው ያልነው ነገር በሌላ ጊዜ ምአዲስ ትችት ሂስ እና ዳኝነት ሲለወጥ ህጉም አብሮ የሚለወጠው:: የህግ ባለሞያዎች ጥሩ ህግ የራሱን ሞት ይመኛል ይላሉ ይህም ማለት ማንኛውም የህግ አንቀጽ ራሱን ለሌላ ዳኝነት ክፍት አድርጎ የሚጠብቅ ነው ማለት ነው::

ለምሳሌ:- በአገራችን የቀድሞ ህግ ለልጅ የአባትነት እውቅና የሚሰጠው አባት ብቻ ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ የልጅ አባትነትን በተመለከተ ለሚነሳ ውዝግብ ህጉ ዳኝነት የሚሰጠው የልጅ አባትነትን የሚያውቀው አባት ብቻ ነው በሚል ዳኝነት ላይ ተመርኩዞ ነው:: አሁን በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ለልጅ የአባትነት እውቅና የሚሰጠው አባት ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ምስክርነትን እውቂያ በመስጠት ላይ የተመረኮዘ ዳኝነት ነው:: ይህም የህግ መሻሻል እና እደሳ ሊመጣ የቻለው ከውይይት ከትችት ከጥናት እና ከምርምር ነው:: ሰሞኑን ከፍትህ ሚኒስነር እና ከመንግስት ሚዲያ አዳባቢ የወ/ት ብርቱካንን ጉዳይ በሚመለከት መናገር መጻፍ ዳዡቀዡቀ ነው የሚል አይነት አቀራረብ የዜጎችን መብት በእጅጉ የሚጋፋ ብቻ ሳይሆን ለጤናማ ህግ መኖር አስፈላጊ የሆነውን አየር ማፈንም ነው::

## III ይቅርታ ከሞራል እና ከፖለቲካ አኩዋያ

ቅጣት እርማት እና ይቅርታ ከወንጀል ድርጊት ወይም ከጥፋት በኋላ የሚነሱ ነገሮች ናቸው:: ስለሆነም ቅጣት እና እርማት የተፈጸመውን በደል ለማቃናት በህግ ላይ በመመርኮዝ ከዚ-ፍትሀዊነት ወደ ፍትሃዊነት የሚወሰድ እርምጃ ነው:: ይቅርታ ግን በይዘቱ ከህግ ክበብ ውጭ ያለ ነገር ነው:: ይቅርታ እንደ ህግ ለተፈጸመ በደል ተመጣጣኝ ቅጣት የሚሰጥ ሳይሆን ከሞራል ትሩፋት ተነስቶ በደልን በመሻር ወደፊት ለማየት እና ለመራመድ የሚያስችል እሴት ነው::

ይህን ስንል የተፈጸመው በደል በተበዳይ ላይ የጣለውን መጥፎ ትውስታ በማሻር ተበዳዩ ከተበዳይነት ስሜት ተላቆ ቀጣይ ህይወቱን እንዲመራ የሚያደርግ ነው:: ከዚህ ፍሬ ሀሳብ ስንነሳ ይቅርታ የሚለግሰው ማነው? የሚለው ጥያቄ የግድ መነሳት አለበት:: ወ/ሪት ብርቱካን የፈረመችውን በሽማግሌዎች የቀረበ ሰነድ ስንመለከት ይቅርታ ያለችው የኢትዮጵያን መንግስትና የኢትዮጵያን ህዝብ ነው:: ይቅርታው ተነስቷል ሲባል ግን በሰነዱ ይቅርታ ሰጪ ተደርጎ የተቀመጠው አንደኛው ክፍል ማለትም የኢትዮጵያ ህዝብ ለወ/ት ብርቱካን የሰጠውን ይቅርታ አላነሳም::

የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ወ/ት ብርቱካን በይቅርታ ህጉ መሰረት ያልተሰጣት የ20 ቀን ማስረጃ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ እንዲሰጣት ወደ እናቷ እና ወደ እናትነቷ ተመልሳ ለቦርዱ ያላትን መልስ እንድትሰጥ ቢደረግ አጠቃላይ የማህበረሰብ ጥቅም «common good» ይከበራል የሚል እምነት አለኝ::

---